የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ
NATIONAL ELECTION BOARD OF ETHIOPIA

ቁጥር ኮ/1162/11/829
ቀን ታሕሣስ 25 2015

**ለቦሮ ዲሞክራቲክ ፓርቲ(ቦዴፓ)**
**<u>አሶሳ፣</u>**

**ጉዳዩ፤ <u>የፓርቲው ጠቅላላ ጉባኤ በድጋሚ እንዲደረግ ቦርዱ የሰጠውን ውሳኔ ስለማሳወቅ</u>**

ፓርቲው በመጋቢት 10 እና 11 2014 ዓ.ም ዓ.ም ያካሄደውን ጠቅላላ ጉባኤ በተመለከተ በ19/07/2014 ዓ.ም በቁጥር ቦ/ዴ/97/14 በተጻፈ ደብዳቤ ሪፖርት ማቅረባችሁ ይታወቃል።

ቦርዱ በታህሳስ 19 ቀን 2015 ዓ.ም ባካሄደው ስብሰባ ፓርቲው ከሪፖርቱ ጋር አያይዞ ያቀረባቸውን ሰነዶች ከሕጉ፤ከፓርቲው መተዳደሪያ ደንብ እና የቦርዱ ታዛቢዎች ካቀረቡት ሪፖርት አንጻር መርምሯል።

**1. ጠቅላላ ጉባኤን በተመለከተ**

1.1. በፓርቲው ጉባኤ የተካሄደው የማዕከላዊ ኮሚቴ፣የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ፣የቁጥጥር ኮሚሽን፣የሊቀመንበር እና የም/ሊቀመንበር የምርጫ አፈጻጸም ስርአት በአዋጅ ቁጥር 1162/2011 አንቀጽ 74(3) መሰረት ግልጽ፣ነጻና ፍትሀዊ እንዲሁም በሚስጥር ደምጽ ያልተከናወነ በመሆኑ፤

1.2. የፓርቲውን ሊቀመንበር እና ም/ሊቀመንበር የመምረጥ ስልጣን በተሻሻለው የፓርቲው መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 13.2 መሰረት የማዕከላዊ ኮሚቴው ቢሆንም ፓርቲው ግን ምርጫውን ያካሄደው በስራ አስፈጻሚ ኮሚቴው አማካኝነት መሆኑ የመተዳደሪያ ደንቡን በግልጽ የሚጥስ በመሆኑ፤

1.3. የፓርቲውን ሊቀመንበር እና ም/ሊቀመንበር የመምረጥ ስልጣን በተሻሻለው መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ መሰረት የማዕከላዊ ኮሚቴው ቢሆንም ፓርቲው ግን ምርጫውን ያካሄደው በስራ አስፈጻሚ ኮሚቴው አማካኝነት መሆኑ የመተዳደሪያ ደንቡን የሚጥስ በመሆኑ ፓርቲው ሕጉን መሰረት በማድረግ በድጋሚ የጠቅላላ ጉባኤ ሊያካሂድ እንደሚገባ ቦርዱ ወስኗል።



አድራሻ - ቦሌ ከፍላሚንጎ
ሬስቶራንት ገባ ብሎ በስተቀኝ
አዲስ አበባ ኢትዮጵያ

ስልክ
+251 115 153468

ፋክስ
+251 115 510025

ፌስቡክ
/national-electoal-board-of-ethiopia-nebe

ትዊተር
@NEBEthiopia

ኢሜይል
contact@nebe.org.et

ድረ-ገጽ
www.nebe.org.et

## 2. የተሻሻለ መተዳደሪያ ደንቡን በተመለከተ

2.1 ከአዋጅ ቁጥር 1162/2011 አንቀጽ 74(1)(ሰ) በተጣጣመ መልኩ የጠቅላላ ጉባኤ ለማካሄድ እንዲቻል ቢያንስ 200 የጉባኤ አባላት መገኘት ያለባቸው መሆኑን በሚያረጋግጥ መልኩ ተሻሽሎ ሊቀርብ ይገባል፤

2.2 የፓርቲው የውስጥ አለመግባባቶች የሚፈቱበት ስርአት በአዋጅ ቁጥር 1162/2011 አንቀጽ 74(1)(ሐ) መሰረት በደንቡ ውስጥ ተካቶ ሊሻሻል ይገባል፤ እንዲሁም

2.3 የፓርቲው አባላት ለአገር አቀፍና በየደረጃው ላሉ ምርጫዎች የሚታጩበት ስርአት በአዋጅ ቁጥር 1162/2011 አንቀጽ 74(1)(ቸ) በተመለከተው መልኩ በደንቡ በማካተት ሊሻሻል ይገባል።

**በዚህም መሰረት:-**

ሀ/ ፓርቲው ይህ ውሳኔ ከተገለጸበት ከታህሳስ 25 ቀን 2015 ዓ.ም ጀምሮ በ4 ወራት ጊዜ ውስጥ ማለትም እስከ ሚያዚያ 25 ቀን 2015 ዓ.ም ድረስ ጠቅላላ ጉባኤውን እንዲያካሂድ፤

ለ/ በተለያዩ ደረጃ የሚገኙ የፓርቲው አመራር አከላት ምርጫን በአዋጅ ቁጥር 1162/2011 አንቀጽ 74(3) በተመለከተው መሰረት ግልጽ፣ነጻና ፍትሀዊ እንዲሁም በሚስጥር በሚሰጥ የድምጽ አሰጣጥ ስርአት ብቻ እንዲያከናውን፤

ሐ/ የፓርቲው አመራር አካላት ምርጫ ሲካሄድ በፓርቲው መተዳደረሪያ ደንብ የተቀመጠውን ስርአት በተከተለ መልኩ እንዲያከናውን፤

መ/ ፓርቲው ከላይ በተራ ቁጥር 2 የተመለከቱትን የመተዳደሪያ ደንብ ማሻሻያ የሚያስፈልጋቸው ክፍሎች ላይ ረቂቅ ማሻሻያ በማድረግ የጠቅላላ ጉባኤው ከሚካሄድበት ቀን 5 የስራ ቀናት አስቀድሞ ለቦርዱ እንዲያቀርብ፤

ሠ/ ፓርቲው የጉባኤውን ዝርዝር ሂደት እና ውሳኔ የሚገልጽ ቃለ ጉባኤ፣ በጉባኤው የጸደቀውን መተዳደሪያ ደንብ እና የጠቅላላ ጉባኤው ሪፖርት ጉባኤው በተካሄደ በ15 ቀናት ውስጥ እንዲያቀርብ ቦርዱ የወሰነ መሆኑን እናሳወቃለን።

ከአክብሮት ሠላምታ ጋር

ውብሸት አየለ ጌጤ
Woubshet Ayele Gete
Deputy Chairperson National Electoral Board